**ሸም ወላዲ ናይ አፄ ቴዎድሮሰ ንምንታይ እዩ ዘይፅዋዕ?**
**ብ Yemane Abadi Mekelle**

**ትግራዋይ_እዮም !**
**የአጼ #ቴድሮስ_ሃይለጅወርግስ_ወልደጅወርግስ ማንነትና የቅማንት ማንነት በጥቂቱ**

አፄ ቴድሮሰ ከትግራይና ከቅማንት ብሔር ተወላጆች የተገኙ ጀግና ናቸው። አጼ ቴድሮስ የተወለዱት #ከትግራዋይ አባታቸው #ሃይለጅወርግስ -ወልደጅወርግስና ከቅማንት እናታቸው ከወይዘሮ ትሻል ካሳ በዳዋ ዳሞት በሚባለው የቅማንት ቀበሌ ነው። የአጼ ቴድሮስ የማንነት ጥያቄና የሀገራችን ታሪክ ጸሐፍት ቅጥፈት......... ሁሌም የሚገርመኝ፤ አንዳንዴም የሚያሳዝነኝና የሚያሳፍረኝ የኢትዮጵያችን ታሪክ በውሸት፣ በቅጥፈት፣ በዘረኝነትና በወገንተኝነት የታጨቀ መሆኑ ነው። የሀገራችን የታሪክ ጸሐፊዎች ነን ባዮች ከጎሳ፣ ከሃይማኖት፣ ከፖለቲካና ከአካባቢ አንጻር እየቃኙ ታሪካችንን አበላሽተውታል። ነገሥታቱንና የተወሰነውን የሕብረተሰብ ክፍል ለማስደሰት ሲሉ አኩሪ ታሪካችንን ጥባጥቤ ተጫውተውበታል። ከ ወር በፊት በለጠፍኩት አጭር ጽሁፍ ላይ ጓደኞቼ ስለ ዳግማዊ አጼ ቴድሮስ ማንነት የሚመለከት አስተያየት ሰጥተው ነበር። ሁልጊዜ ጥያቄ ከሚጬሩብኝ የታሪክ ጉዳዮች መካከልም የአጼ ቴድሮስ ጉዳይ አንዱ ነው። እስኪ ልጠይቃችሁ

የአጼ ቴድሮስ ወላጅ አባት ታሪክ ብዙ አይታወቅም፤ ለምን? የሰው ልጅ ካለ አባት ልክ እንደ ዶሮ በንፋስ ይወለዳል እንዴ?

በታሪክ እንደተማርነው ከሆነ አጼ ቴድሮስ የኮሶ ሻጭ ልጅ በሚል መጠሪያ ነው የሚታወቁት። የሃይለጅወርግስ ወልደጅወርግስ ልጅ ሲባሉ ሰምቼም አንብቤም አላውቅም። የተወሰኑ የአማራ ጓደኞቼን የአጼ ቴድሮስ አባት ስም ማን እንደሚባል ጠይቄያቸው ነበር። እነሱ የሰጡኝ ምላሽ "አባቱ ማን እንደሆነ አይታወቅም" የሚል ነበር።

ግን ለምን አባታቸው አይታወቁም ካልን አባታቸው የትግራይ ተወላጅ ስለሆኑ ብቻ የታሪክ ጸሐፍቶቻችን ሆን ብለው ታሪካቸው እንዲነሳ ስለማይፈልጉ የሚል ነው።

ታሪኩ በአጭሩ እንዲህ ነው። አቶ ሃይለጅወርግስ የሰው ሕይወት አጥፍተው ትግራይ ተምቤን አካባቢ የሚገኘውን ቀያቸውን ትተው ወደ ጎንደር የሸሹት ገና በወጣትነት ዕድሜያቸው ነበር። ያኔ የቅማንት ብሔር ተወላጅ ከሆኑትና በብሔራቸው ምክንያት ኮሶ ሻጭ የሚል ስም ከወጣላቸው ወይዘሮ ትሻል ጋር ጋብቻ ፈጽመው አጼ ቴድሮስን ወልደዋል። ግራ የሚያጋባው ነገር ወይዘሮ ትሻል ከመሳፍንት ቤተሰብ የተገኙ እንደሆኑ አድርገው የጻፉ ተመልክቻለሁ። ከመሳፍንት ቤተሰብ የተወለደ ኮሶ ይሸጣል እንዴ? ሌሎች ደግሞ የአጼ ቴድሮስ የማንነት ጥያቄ እየተነሳ ሲመጣ ነገሩን ለማስተባበል ሲሉ ለዘመናት ተረስተው የቆዩትን አባታቸውን የደምቢያ አስተዳዳሪ እንደነበሩ በድረገጾች መጻፍ ጀምረዋል። ሆኖም አቶ ሃይለጅወርግስ ደምቢያን ይቅርና ትንሽየ ቀበሌን እንኳ ያላስተዳደሩ ይልቁንስ በጎንደሮች ዘንድ የትውልድ ቀያቸውን ለቀው የመጡ ባይተዋር መጤ ነበሩ።

እሺ እንደ ታሪክ ጸሐፊዎቹ ይሁንና የአጼ ቴድሮስ አባት ደምቢያን የሚያስተዳድሩ መስፍን ሆነው እንዴት ነው ኮሶ ሻጭን ሊያገቡ የቻሉት። በዚያ ትውልድንና አጥንትን ተቆጥሮ ጋብቻ ይፈጸምበት በነበረው ዘመን ሁለት የተለያየ የኑሮ ደረጃ ያላቸው ሰዎች እንዴት ሊጋቡ ቻሉ? በቃ የኢትዮጵያን ታሪክ ስታነቡት እንደዚህ ዓይነት ብዙ እርስበርሱ የሚጣረስ ታሪክ ታገኛላችሁ። ይኼ ሁሉ የታሪክ መዘበራረቅ ከየት የመጣ ነው ካልን ታሪክን በአግባቡና በእውነት ካለመሰነድ የመጣ ነው የሚል ነው። እዚህ ጋር የንጉሡ አባትና እናት ታሪክ ብቻ አይደለም ተዳፍኖ እንዲቀር የተደረገው። የአጼ ቴድሮስ ሁለተኛ ሚስት የነበሩት የንግስት ጥሩወርቅ ውቤ (የትግራይ አገረ ገዥ የነበሩት የደጃች ውቤ ሃይለማርያም ልጅ) ታሪክም ሲነሳ አናይም። ብዙ የተወራለት ልዑል አለማዮሁ ቴድሮስን የወለደች ውቧ ጥሩወርቅ የትግራይ ተወላጅ ስለሆነች ብቻ የንግስትነት ክብሯን እንድትነፈግ ሆኗል። ለምን ታሪክኮ ታሪክ ነው። ወደድንም ጠላንም ከታሪክ ተጠያቂነትኮ አናመልጥም።

ቅማንትና አጼ ቴዎድሮስ
^^^^^^^^^^^^^^^^^^^^^^^^

ስለ ቅማንት ብዙ የተጻፉ መረጃዎችን ማግኘት በጣም አስቸጋሪ ነው። ተፅፈው የሚፈኙትም ቢሆኑ በወቅቱ በነበረው ማህበራዊና ፖለቲካዊ ማዋቅሮችና አስተሳሰቦች ተጽዕኖ ሥር ስለነበሩ ገለልተኛ በመሆን የተጻፉ መረጃዎችን ማግኘት የሚቻልበት እድል በጣም አነስተኛ ነው። የውጭ ጸሐፍት እንኳ ቢሆኑ ከዚህ ችግር ርቀው የጻፉት በጣም ጥቂት ናቸው። ምክንያቱ ደግሞ መረጃውን የሚሰበስቡት በአብዛኛው ጊዜ ከላይ በተቀስኳቸው ማህበራዊና ፖለቲካዊ ስነ ምህዳሮች ተጽዕኖ ሥር የነበሩ ግለሰቦችን ወይም ድርድቶች ስለሆኑ ነው።

***

የታሪክ ማህደራትን ስናገልብጥ ከምናተኩርባቸው ጉዳዮች መካከል "ቅማንት እንደሌሎች መጤ ሕዝብ ነው ወይስ ነባር ኢትዮጵያዊ?" የሚለው ጥያቄ ሲሆን ይህም በአብዛኞች ታሪክ ጸሐፍት ዘንድ ልዩነት ፈጥሮ ይገኛል። አንዳንዶቹ "ቅማንት ቀደምት ኢትዮጵያዊ ህዝብ ነው" ሲሉ፤ ሌሎች ደግሞ "ከመካከለኛው ምሥራቅ ተሰዶ የመጣ" እንደሆነ አድርገው ይከራከራሉ። ቅማንት ከመካከለኛው ምሥራቅ ተሰዶ እንደመጣ ከሚተርኩ ሰዎች መካከል አለቃ አጽሜ አንዱ ነው።

***

በአለቃ አጽሜ ትረካ ውስጥ መዘባረቆች ይበዛሉ። ለምሳሌ ይህን እንመልከተው፦ "ቅማንት ነባር ሕዝብ እንጂ መጤ አይደለም፤ ቅማንት የቀድሞ ሕዝብ ነው። የመጣውም ከሙሴ በኋላ የእስራኤል ትራፊ ይመስላል [ከዚህ ላይ ልብ ልንል የሚገባን ነገር ቢኖር የሚጽፉት በይመስለኛል እንጂ በመረጃ ተደግፎ እንዳልሆነ ነው]። ከዚህ አባባል ውስጥ ሁለት የማይጣጣሙ ሃሳቦች እንዳሉ መገንዘብ ጥሩ ነው። በአንድ በኩል "ቅማንት መጤ አይደለም ነባር ሕዝብ ነው" ይላል፤ በሌላ በኩል ደግሞ ቅማንት እነሙሴ እስራኤላዊያንን መርተው ከግብጽ የባርነት ኑሮ ነጻ አውጥተው ወደ ተስፋይቱ ምድር ሲወስዱ የተረፈው ሕዝብ ማለትም "ቅማንቱ" የዓባይን ፈለግ ተከትሎ ወደ ኢትዮጵያ መጥቷል ይለናል። ይህ ማደባለቅ የቀደምት ታሪክ ጸሃፍት ተጠየቅ አያውቁም ብለን ከማለፍ ውጭ ምን ይባላል?

***

አለቃ አጽሜ ይቀጥልና እንዲህ ሲል ያብራራል፦ "የቅማንት አምልኮውም ቋንቋውም ልዩ ነው። . . . የአገው፣ የፈላሻ . . . የጀበርቴ [ብሌን] ቋንቋ ይመስላል። ደግሞ የላስታ፣ አገውና በበጉስም ያሉ አገዎች ቋንቋቸው ይመሳሰላሉ። እንዲያውም ዘመዳሞች ናቸው፤ ይጠያየቃሉ። . . . አገው ግን የመጣበትን ጊዜ ምልክቱን አጣነው።" በእርግጥ የቅማንቱን ታሪክ በእርግጠኛ ሳያውቅ በመሰለኝ የጻፈ አለቃ አጽሜ የአገውን ሕዝብ ታሪክ በትክክል ይጽፍ ዘንድ እንዴት ይቻለዋል? ይህን የህሊና ዳኝነት ለአንባቢያን ትቼ ሌላውን ልቀጥል። አለቃ አፅሜ ቀደም ሲል "ይመስላል" ብሎ ተናግሮ አሁን ደግሀ እንዲህ ይለናል፦ "በሙሴ ጊዜ የመጡ ቅማንት ተባሉ ከባቢሎን ምርኮ በኋላ የመጡ ፈላሻ ተባሉ።" መቼም ይህ ከአፈ ታሪክ ያልዘለለ ተረት ተረት እንጂ እውነት ሊሆን ይችላል ብሎ ማመን ሞኝነት ነው። ሰውየው ይህን የይሆናል ሃሳብ የገመተው "ፈላሻና ቅማንት በቋንቋ አይለያዩም ... በአምልኮ ብቻ ይለያያሉ።" በሚለው ክርክሩ ላይ ተንተርሶ እንደሆነ መገመት አያዳግትም። ሕዝቦች ተመሳሳይ ቋንቋ በመናገራቸው ከአንድ የዘር ግንድ ተቀድተዋል ብሎ መደምደም የዋህነት ነው። ለምሳሌ ከጋፋት የመጣውን የደቡብ ጎንደር አማራ፣ ከኦሮሞ የመጣውን የሜጫ ጎጃም አማራ፣ ከቅማንት የመጣውን የደንቢያ፣ አለፋና ጣቁሳ አማራ፣ ከዳሞት የመጣው የፍኖተ ሰላም አማራ፣ ወዘተ አማርኛ ስለተናገረ ብ ቻ ከአንድ ዘር የመጣ ሕዝብ ነው ብሎ ማመን ይቻላል? በእርግጥ አማራ የሚለውን በሔር መቃወሜ አይደለም። አማራ የሆነ አማራ የመሆን መብቱ የተጠበቀ ነው። እስኪ ንቡረ እድ ኤርሚያስ ከበደ ስለ አማራነትና አማራ አፈጣጠር የጣፉትን የመጽሐፋቸውን ክፍል አንብቡት።

***

አለቃ ታዬ ገ/ማርያምም በበኩሉ ቅማንት የሚባለው ሕዝብ ከነገደ ኦሪት (እስከ ጥፋት ዉኃ ድረስ የነበረ ነገድ እንደ ሆነ ይተርካል) ቀጥሎ ከመጣው ነገደ ካም ለጥቆ የመጣ ሕዝብ እንደሆነ አድርጎ ይነግረናል። እንደ አለቃ ታዮ አባባል ካም ከልጆቹ ጋር ከእስያ በባብ ኤልመንደብ በኩል ተሻግሮ በ2787 ዓመተ ዓለም ወደ ኢትዮጵያ እንደገባና 78 ዓመታት ከነገሠ በኋላ እንደገና ተመልሶ ወደ እስያ ተሻግሮ በመሄድ ሶርያን ለመያዝ ከሴም ጋር ሲዋጋ ስለሞተ ልጆቹ ታላቅ ወንድማቸውን ኩግን አንግሠው ኢትዮጵያን ወርሰዋል ይለናል። በዚህም ሁኔታ ለአያሌ ዓመታት ኖረዋል

ይለንና እንዲያውም በዚህ በነገደ ካም ዘመነ መንግሥት ነገደ ሻንቅላ፣ ነገደ ቅማንትና ነገደ ወይጦ ወደ ኢትዮጵያ እንደገቡ ያትታል። ልብ በሉ፦ ካም፣ ልጆቹና የልጅ ልጆቹ ኢትዮጵያን ወርሰውና ነገሠው እንደኖሩ ከነገረን በኋላ እነዚህ ቆይተው መጡ የተባሉት ደግሞ የካም ልጆች እንደሆኑ ያስረዳናል። ነገር ግን ይሄን ሃሳብ ስትመለከቱት አልተወዛገበም ትላልችሁ? እንዲያውም ይውጣላችሁ ብሎ አራተኛው የካም ልጅ ሐማቴ ወደ ኢትዮጵያ የገባው በነገደ አግዓዝያን ዘመን ነው ይለናል። ይሁን ብለን እንለፍና ስለ ቅማንት ምን እንደሚል እንመልከተውና እንገምግመው።
***
ከክርስቶስ ልደት በፊት 2410 ዓመታት ገደማ የቅማንቶች አባት የከነዓን የልጁ ልጅ (የአርዋርዲ ልጅ) አይነር የቅማንቶች አባት ከከነዓን አገር ተሰዶ ወደ ኢትዮጵያ እንደመጣ ይተርካል። ይህም የሆነው በከነዓን ምድር ረሃብ በፀና ጊዜ ነበር ይለናል። ይህም ቢሆን ከላይ እንዳነሳሁት እርስ በእርሱ የሚጣረስ ነው። በአጠቃላይ አለቃ ታየም ሆነ አለቃ አጽሜ ለጽሑፋቸው ግባት አድርገው የተጠቀሙት “ክብረ ነገሥት” የተባለው መጽሐፍ እንደ ሆነ ልብ ይሏል። ይህ መጽሐፍ ደግሞ የቀደሙ ሰሎሞናዊያን ነን ባዮች እንደሚመቻቸው አድርገው የሌሎችን ታሪክ የጻፉበት እንጂ በትክክልኛ መረጃ ላይ ተደግፈው እንዳልጻፉት ይታወቃል። ሰሎሞናዊያኑ የሚያስጨንቃቸው የዘር ንግሥናቸው እንጂ እውነት አልበረም። ንጉሥ የሚባለው ሁሉ ከሰሎሞን ዘር ጎትቶ የማገኛት አበዜ የተጠናወታቸው ነበሩ። ሁሌም እነሱን ከፍ ከፍ የሚያደር ነገር ብቻ ነበር የሚጽፉት እንጂ የቅማንቱን ነባርነት እንዴት አድግርው ሊያወሩት ይችሉ ነበር?
***
ሁለተኛው ሃሳብ ደግሞ “ቅማንት መጤ ሳይሆን ነባርና ጥንታዊ ሕዝብ ነው” የሚለው ሲሆን፤ አንዳንድ ተመራማሪዎች የበኩላቸውን ብለዋል። ለምሳሌ ቶወርነይ (2009) የተባለው ሰው ቅማንት የሰሜናዊ ኢትዮጵያ ማዕከላዊ ክፍል ነባር ሕዝብ እንደሆነ ሲናገር እንዲህ ብሏል፦ The Kemant Agew people are considered as the original inhabitants of central-northern Ethiopia. . . live in the Gondar area. . . [they] are descendants of Cushetic-speaking Caucasoid hunters. . . . እነዚህን ቀደምት ሕዝቦች ብላክ (1869) የተባለው ጸሐፊም “ከማውንት” ብሎ ይጠራቸዋል።ልክ ጀምስ ብሩስ የተባለው የእንግሊዝ ሰላይ “ከሞንት” ብሎ እንደጠራቸው ማለት ነው። የሚኖሩትም ከጣና ሰሜን ምዕራብ በሚገኝ ጭልጋ በሚባለው አውራጃ እንደነበር ብላክ ያስቀምጣል። በእርግጥ የቅማንቶችን መኖሪያ አለቃ ታዬ ዘርዘር አድርጎ ስላስቀመጠው ጭልጋ ብቻ ነው ብሎ መቀበል ሞኝነት ነው። እንደ አለቃ ታየ መረጃ ከሆነ ቅማንቶች የሚኖሩት በከርከር፣ ጃኒ ፈንቀራ፣ ቦበካ፣ ጋባ ጋላገር፣ ከሰየ፣ ጭልጋ፣ ወዘተ ነው እንጂ በጭልጋ ብቻ አልነበረም። እንዲያውም የቅማንት መነሻው ከርከር እንደሆነ ይተረካል። እንደ ፍሬድሪክ ጋምስ ከሆነ ደግሞ ቅማንቶች የጎንደርን ከተማን ከበው እንደሚገኙ ግልጽ ነው። በእርግጥ ጎንደር የቅማንቶች የሕገ-ልቡና ቅዳሴ የሚቀደስበትና ማዕካላዊ ቦታቸው እንደነበር ቢታወቅም በኋላ ወደ ቦታው የመጣው የሰሎሞናዊው ሥርወ መንግሥት ይህን ቦታ ከቅማ   ቶች ቀምቶ የንግሥና ማዕከል አድጎ በመያዝ ቅማንቶችን በራሳቸው ርስት ባይተዋር አድርጓቸዋል። እንዲያውም ይብስ ብሎ “ቅማንት የንጉሡን ድንኳን ለመሸከምና ለመትከል ንጉሡን ተከትሎ እንደመጣ” አድርገው የእውር ድንብስ ታሪክ ጻፉለት። መቼስ ጊዜ የሰጠው ቅል ድንጋይ ይቆረጥማል አይደል የሚባልው።
***
ፍሬድሪክ ጋምስ ቅማንት የጥንት ሕዝብ እንደሆነ በትክክል አስቀምጧል። By 5000 B. C. and probably well before, Bushmanoid and Caucasoid hunters and gatherers occupied the Ethiopian plateau and surrounding areas. The Caucasoid hunters and gatherers undoubtedly were the ancestors of the Cushitic speaking peoples of present-day Ethiopia, including the Qemant. ማለትም “በ5000 ዓመተ ዓለም (ምናልባትም ከዛ ቀደም ብሎ) የቡሽማኖይድና ካውካሰይድ አዳኞችና ፍራፍሬ ለቀሚዎች የኢትዮጵያን ተራራማውን ቦታና አካባቢው ይዘውት ነበር። የካውካሰይድ አዳኞችና ፍራፍሬ ለቃሚዎች በእርግጠኝንት አሁን በኢትዮጵያ ለሚገኙ የኩሽ ቋንቋ ተናጋሪ ሕዝቦች (ቅማንትን ጨምሮ) የዝርያ ግንዶቻቸው ነበሩ።” በእርግጥም ከላይ ካነሳሁት መረጃ ይህኛው በተሻለ የቅማንትን ወይም የኩሽ ሕዝቦችን ነባርነት ያብራራል ማለት ያስደፍራል።
***
ከዚህ ላይ ሌሎችንም መረጃዎች እያነሳን አስፍተን ማየት ቢቻልም ለጊዜው ለውይይት መነሻ ይሆን ዘንድ ያነሳሁት በቂ ነው እላለው። ነገር ግን ሳልጠቅስ የማላልፈው ጉዳይ ቢኖር ቅማንት ነባር ሕዝብ እንጂ አንዳንድ የራሳቸውን

ታሪክና ባህል ሙልጭ አድርገው አጥፍተው የቅማንቱን እየዘረፉ በማናለብኝነት የራሳቸው አድርገው የኖሩ ታሪክ ዘራፊ ህዝቦች አባላት የሆኑት ሊሂቃንና ምሁራን ተብየዎች የራሳቸውን ታሪክ ለመካብ የቅማንቱን ታሪክ ሆን ብለው ሲበርዙትና ሲያጠፉት ለዘመናት መኖራቸውን ነው። ነገር ግን ፍሬድሪክ ጋምስ እንደሚለን (several agew groups, including the Qemant, remained culturally distinct and did not lose their identity in the growing population of the Amhara) ቅማንትን ጨምሮ ብዙዎቹ የአገው ሕዝቦች በባሕላቸው ልዩ ሆነው ቆይተዋል እናም እያደገ በመጣው የአማራ ሕዝብ ምክንያት የራሳቸውን ማንነት አላጠፉትም። በእርግጥም እስከ አሁኑ ይዘውት ዘልቀዋል። ቅማንትን ብናየው ያን ሁሉ የከፋ የባህልና ማህበራዊ ጫና ተቋቁሞ እስከ 21ኛው ክፍለ ዘመን በመዝለቅ ዛሬም ማንነቱን እያስከበረ ይገኛል።
***
የአገው ሕዝቦች ክህነትን ከአባቶቻቸው ከእነ መልከ ጸዴቅና ዮቶር የመንግሥት አወቃቀርንና አስተዳደርን ከአባታቸው ከካም ወርሰው እርስታቸውን ኢትዮጵያን መስርተው የኖሩ ቀደምት ሕዝቦች ሲሆኑ እንደ ፍሬድሪክ ጋምስ ከሆነ በሰባት ይከፈላሉ። እነሱም ቅማንት፣ አዊ፣ ኩንፈል፣ ህምራ፣ ብሌን፣ ዳሞት እና ህምጣ ናቸው። እነዚህ ሕዝቦች በታሪክ ሂደት በተፈጠረባቸው ጫና በአንድ በተያያዘ መልክዓ ምድር ከመኖር ተነጣጥለው በየ አገሩ እንዲኖሩ ተደርገዋል። በመካከላቸው የአማራ ጉልተኛ እርስት እየሠራ ስለገባባቸውና አብዛኛውን ሕዝባቸውን አማራ ስላደረጉባቸው ህምራው ከቅማንቱ፣ ቅማንቱ ከአዊው፣ እንዲሁም ከሌላው ወንድሙ ጋር ተለያይቶ እንዲኖር ተደርጎ ቆይቷል።
***
በወቅቱ እያቆጠቆጠ የመጣው አማራነት የእነዚህን ሕዝቦች ታሪክና ባህል እየወሰደ ከአዲሱ ባህል ጋር በማዋሃድና በማጣጣም ተጠቅሞበታል። ለምሳሌ የቅማንት የሕገልቡና እምነት ውስጥ የሚገኙ አያሌ ነገሮች ወደ ክርስትናው ተወስደው አገልግሎት በመሥጠት ለይ እንደሆኑ ማየት ይቻላል። በተለይ ደግሞ የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ትውፊትና ሥርዓት በዓለም ካሉ ሌሎች ተመሳሳይ አኃት አቢያተ ክርስቲያናት ልዩ የሚያደርጋት ይኸው ከአገው ህዝቦች የወረሰቻቸው ትውፊቶችና አሰራሮች ናቸው። ለምሳሌ የመስቀል ደመራ በዓል፣ የካህናት አጠማጠም፣ በቤተክርስቲያን ነጭ ልብስ መልበስ፣ ወረብ፣ በየዓቢያተ ክርስቲያናት አካባቢ ዛፍ መትከል፣ ጸዲቀ መበለት፣ ተስካር፣ የጥምቀት በዓል ማክበር፣ ወዘተን ማየት ይቻላል። ምን ይህ ብቻ ሰሜን ኢትዮጵያ ውስጥ ያሉ ብዙ ድንቅ ድንቅ ሥራዎች እኮ የአገው ሕዝቦች ናቸው። የላሊበላን ውቅር አቢያተክርስቲያናት፣ ሴባስቴፖል፣ አኹሱም፣ ወዘተን ማየት በቂ ነው። ለተጨማሪ ማብራሪያ wonderful Ethiopians ይሰኘውን መጽሐፍ ማንበብ ይቻላል።
***
መቼም ይህን ጉዳይ ሳነሳ ቤተክርስቲያንን እንደነቀፍኩና እንደ አዋረድኩ አድርጋችሁ እንደማትረዱኝ ተስፋ አደርጋለሁ። በእርግጥ ያነሳኋቸው የሃይማቱን ትክክለኛነት ወይም መሳሳት ለመሞገት ሳይሆን የቅማንት ባህል እንዴት ሆኖ እየተወረሰ እንደሄደ ለማሳየትና ቅማንት ወይም ሌሎች የአገው ሕዝቦች ለኢትዮጵያ የነበራቸውንና ያላቸውን ትልቅና የማይናቅ አስተዋጽኦ ለማሳየት እንጂ። ነገር ግን መዘንጋት የሌለበት ጉዳይ ቢኖር “በወቅቱ እነዚህን ነገሮች መውረስ ከተቻል ለምን ከማንተነይ ቋንቋንም አብሮ መወረስ አለተቻለም?” የሚለው ጉዳይ ነው።
***
ከዚህ ቀደም በአንዳንድ መጣጥፎቼ እንዳነሳሁት “ቅማንት ክርስቲያን ሲሆን ለምን ቋንቋውን እንዳይናገር ልዩ ልዩ ግልጽና ስውር ጫናዎች ተካሄዱበት?” በማለት የነበረውን ስህተት አሳይቻለሁ። የክርስትና ቅዳሴ በከመንትነይ ቢቀደስ እግዚአብሔር አይቀበልም ይሆን? ነው ወይስ ከመንትነይ የመላእክት ቋንቋ አልነበረም ወይም አይደለም ማለት ነው? መልሱን ኢትዮጵያዊነትን ላበላሹት ትምክህተኞ ትቸላቸዋለሁ። እነሱ ከክርስቶስ ይልቅ ለድብትርናው፤ ከመስቀሉ ይልቅ ትላንት ለፈጠሩት ባንዴራ፤ ከሰው ይልቅ ለመሬት፤ ከእውነትና ትህትና ይልቅ ሐሰትና ትእቢትን እያስቀደሙ በመኖራቸው ሃገራችንን በፊት ስልጣኔን ጀምራ የዓለምለም መጨረሻዋ ድኃ ሆና እንድትኖር ያደረጉ ደግኖች ናቸውና ይህን ጉዳይ በተለመደው ቆርጦ ቀጥል ምላሳቸው ያብራሩልን።
***

አጼ ቴዎድሮስ ቅማንት ወይስ ሌላ?
********************************

ስለቅማንት ሕዝብ ይህን ያክል ካልኩ ከዚህ ቀደም አጼ ቴዎድሮስ ቅማንት መሆኑን አንስቼ በጻፍኩት አጭር መጣጥፍ ላይ አንዳንድ እንደ ተሸፋፈኑ መቀጠል የሚፈልጉ ሾላ በድፍኑ የሆኑ ወገኖች ብዙ ሰድበውኛል፡፡ አንዳንዶቹም “መረጃ የለሕም፤ ዝም ብለህ ነው የምትቦጠልቀው” ብለውኝ ነበር፡፡ ምንም እንኳ ስለ አንድ ሰው የደም ዝምድና ለመመስከር የሚችለው ያው ዘመድ የሆነው ሰው ቢሆንም የዘመኑ ሰዎች ግን የተጻፈ ነገር ካላመጣህ ስላሉኝ እነሱን ይገባቸው ዘንድ የተፃፈ መረጃ ላቅርብላቸውና ላሳያቸው፡፡ እዚህ ላይ አንባቢያን ልትረዱት የሚገባው ነገር ቢኖር ይህን የማቀርበው እውነትን በመናገርና በማውጣት ታሪክን ለእውነተኛው ባለታሪክ እንዲመለስ ለማድረግ እንጂ ዘረኝነትን ወይም ጥበትን ለማስፋፋት እንዳልሆነ ነው፡፡ ሁላችሁም እንደምታውቁት ቅማንት ምርጥ ኢትዮጵያዊ ነው፡፡ ሳይገባው ከማንም ጋር አይነፍስም፡፡ በገባው ነገር ደግሞ ራሱን አሳልፎ ይሰጣል፡፡
***
ለኢትዮጵያችን በኢኮኖሚ፣ በማህበራዊ፣ በቴክኖሎጂና በፖለቲካ ኋላ ቀርነት የበኩሉላቸውን ድርሻ ካበረከቱት ነገሮች መካከል የነበረንን ታሪክ በትክክል እየዘገብን አለመምጣትና እና አንዱ ንጉሥ ሢነግሥ የቀድሞውን ንጉሥ ታሪክና ተግባራት በቡችሎቹ አማካይነት እየደመሰሰ መምጣቱ ሲሆን በየጊዜው የሚነሱ ጸሐፍትም እውነታውን ከመናገርና ከማጽናት ይልቅ ለራሳቸው ፖለቲካ እንዲመቻቸውና ጌቶቻቸውን እንዲያስደስቱ እያደረጉ መጻፋቸው ነው፡፡ ስለዚህ አጼ ቴዎድሮስ የሠራው ሥራ ከቅማንቱ አልፎ የኢትዮጵያ መኩሪያ እንደ ሆነ ልናምን ይገባናል፡፡ ይህ ደግሞ የሀገር ሀብት እንጂ የሌላ የማንም አይደለም፡፡ ነገር ግን ቅማንትነቱን መደበቅና ከነበረው የሰሎሞናዊው አፋኝ ሥርዓት ጋር ማዋሸም ተገቢ እንዳልሆነ መረዳት ያስፈልጋል፡፡ ለነገሩ ትምክህተኞች የዚህን እውነታ ገሃድ መውጣት ሲያዩ ወይ “ቴዎድሮስ የሚባል ንጉሥ አልነበረም፤ አሊያም ቴዎድሮስ የተባለው ካሳ ሐይሉ ሳይሆን ሌላ ከሰማይ የመጣ ፍጥረት ነው” ማለታቸው አይቀርም፡፡
***
በእርግጥ እስከ አሁንም ድረስ አንዳንድ ቅማንትን የሚሳደቡና የሚያንቋሽሹ ትምክህተኝነት የተጠናወታቸው ግለሰቦች ባይታጡም በተለይ ከደርግ በፊት የነበሩት ሁሉም ሥርዓቶች እንደ ቅማንት ባሉት ጭቁን ሕዝቦች ላይ ታላቅ የማግለልና የማሸማቀቅ ግፍና በደል ይደርስባቸው ስለነበር አይደለም ለመንግሥትነት ለአሽከርነት እንኳ አይመረጡም ነበር፡፡ ነገር ግን አጼ ቴዎድሮስ ይህን ሁሉ ሰብሮ በመውጣት የንግሥናውን ኮርቻ ተፈናጧል፡፡ ንግስና በሥራና ጀግንነት እንጂ በዘር ወይም በደም እንዳልሆነ አሳይቷል፡፡ ኢትዮጵያን በየጎበዝ አለቃው ከፋፍሎ ሲያምስ የነበረውን ትምክህተኛና ደናቁርት ኃይል ድምጥማጡን አጥፍቶታል፡፡ ሆኖም ግን አጼ ቴዎድሮስ ቅማንት እንደሆነ በኩራት አይናገርም ነበር፡፡ ምንም እንኳ አማራም ነኝም ብሎ ባያውቅም፡፡ ደብተራዎችና መተተኞች ሲያሙትና ተንኮል ሲሸርቡበት እንደነበረ ግን በደም ያውቃል፡፡ በብርሃኑ ዘሪሁን የታንጉት ምስጢር ውስጥ የሚገኘውን ደብተራ አክሊሉን አስቡት፡፡ በዚህም ቅማንት መሆን ምን ያክል የሥነልቡና ጫና እንደነበረው ማስተዋል ይቻላል፡፡ ይህን የበለጠ ለመረዳት የታንጉት ሚስጢርን በደንብ ብታነቡት እጅግ ጥሩ ነው፡፡
***
እኔ የምለው ቅማንትነትን ጀግናው አጼ ቴዎድሮስ እንኳ ደፍሮ መግለጽ ያልቻለው ሌላው ተራው ሕዝብማ እንዴት ባለ ጥልቀት ይሸማቀቅ ኑሮ ይሆን? በእርግጥ የዛሬዎቹ ዳግማዊ ቴዎድሮሶች ቅማንትነታቸውን እስከ መስዋዕትነት ከፍለው መስክረዋል፡፡ ቅማንትነታቸውን በደማቸው ፅፈዋል፡፡ ቅማንት ነኝ ማለት በዛሬዎቹ ትምክህተኞች እንኳ ይህን ያክል ከባድ ዋጋ ካስከፈለ በድሮዎቹማ ምን ያክል መከራ አሳልፈውበት ይሆን? በእርግጥ ዘመነ መሳፍንት እየተባለ የሚጠራው የጨለማ ዘመን ቅማንት የሆነው ጀግናው ራስ ካሳ ሐይሉ ወደ ስልጣን እንዲመጣ ታላቅ ድጋፍ ነበረው፡፡ በዋናነት ግን ቅማንት የሚባል ታማኝና ቅን ሕዝብ ተደብቆ እንዳይቀር ለማድረግ እግዚአብሔር የኮሶ ሻጯን ልጅ አስነስቶ ንጉሠ ነገሥት አደረገው፡፡ ምንም እንኳ ደብተራዎችና ጠንቋዮች የቴዎድሮስን ቅማንትነት በማንሳት ውሥጥ ለውሥጥ ተንኮል እየሠሩ እንዲወድቅ ሲታገሉ የነበሩ ቢሆንም፡፡ በእርግጥ ቅማንት ቴዎድሮስ ቴዎድሮስ ቅማንት ናቸው፡፡ ሁለቱም የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጽታዎች ናቸው፡፡ ቅማንት ታታሪነት፣ ታማኝነት፣ ሐቀኝነት እና ጀግንነት ነው፡፡ እነዚህንም ጠባያት በአጼ ቴዎድሮስ ውሥጥ አይተናቸዋል፡፡ በዚህ ብቻ የሚከተለውን መረጃ ሳያዩ ማመን ይቻላል፡፡
***

መቼም በምን መረጃ ተመስርተህ ነው ይህን ያክል ደረትክን ነፍተሕ የምታወራው እንደምትሉኝ ይገባኛል። ራስ ካሳ ሐይሉ ቅማንት ነበር። የተወለደውም በብሔር ጭቆና ምክንያት ህወታቸው ተጎሳቁሎባቸው ነብሳቸውን ለማቆየት ሲሉ እንቆቆና እንጨት እየሸጡ ከሚኖሩ ምስኪን ቅማንት ቤተሰቦቹ ነበር። መቸም ትምክህተኛው እንደሚለው ካሳ ከደጃች ሐይሉ የደንቢያ ባላባት ነበር የተወለደው አልልም። በእርግጥ ደምቢያ አለፋና ጣቁሳ ቅማንት እንደነበሩ ከታች የምናቀርበው መረጃ በግልጽ ያስቀምጣል። የባላባት ልጅ "አባቱ በመሞቱ ምክንያት እናቱ ኮሶ ሸጠች" ብትሉ ማን ይሰማችኋል? በእውነት ለመናገር ቴዎድሮስን በቀጥታ ያ ቅማንት ብለው ለመናገር ስላልደፈሩ "የኮሶ ሻጭ ልጅ" እያሉ አስወሩና ቅማንትነቱ በተዘዋዋሪ አወሩን። እናመሰግናልን። አንዳንዴም የጠላት መረጃ በጣም ጠቃሚ ነው። አጼ ቴዎድሮስ የተወለደው ዳዋ ዳሞት በሚባለው የቅማንት ቀበሌ ሲሆን እድገቱ ግን ከአንዱ ቦታ ወደ ሌላው ቦታ እየተዟዟረ እንደ ነበር አያሌ መረጃዎች ያሳያሉ። በወቅቱ በልዩ ልዩ ምክንያቶች በጭልጋ፣ ከርከርና ቋራ በነበሩ ዘመዶቹ አድጓል። በሌላ ጊዜ በዝርዝር የምመጣበት ስለሆነ ብዙም ማለት አልፈልግም። ነገር ግን አሁን ቴዲ ቅማንት መሆኑን በተመለከተ እነማን ምን ብለዋል? የሚለውን ላቅርብ።

***

በዕውቀቱ ሥዩመ አለቃ አጽሜ ስለ አጼ ቴዎድሮስ የጻፉትን ከአሜን ባሻገር በተኘው መጻሐፉ አንስቶ የቴዲን ቅማንት ጨረፍ አድርጎል አሳይቶናል። "አጼ ቴዎድሮስ. . . ሀገራቸው ቋራ ነው። የዐማራ ዘር አይደሉም። ዐማርኛ ይናገራሉ እንጂ። ቋርኛ የሚባል ቋንቋ አለ። ደግሞ በቋራ እስከ ዛሬ ሦስት ዓይነት ሕዝብ አለበት። አንደኛው ሄራ ይባላል. . . ሁለተኛው ፈላሻ. . . ሦስተኛው ቅማንት [ሲሆን] በደንቢያ፣ በአለፋ፣ በጣቁሳ አለ። እሳቸው [አጼ ቴዎድሮስ] በነገሡ ጊዜ ከጥንት ሆኖ የማያውቀውን ቅማንቶችን ሾሙ፤ አከበሩ። እነ ደጃች ጣዩን እነ ደጃች ገልሞን ቅማንት እጅግ ያከብራቸውና ያምኗቸው ነበር። ዐማራንና ክርስቲያንን አይወዱም ነበር።" ብሎናል። አንድ ነገር ልብ ልትሉ ይገባል። አለቃ አጽሜ በአጼ ቴዎድሮስ ዘመን የነበረ ታሪክ ጸሐፊ ነው። የጻፈውም ያየውንና በቅርበት የሰማውን እንጂ ፈጠራ ፈጥሮ አልነበረም። ከዚህ በላይ መረጃ ማቅረብ ያስፈልጋል ብየ አላምንም።

***

ከዚህ ጋር በተያያዘ ጀምስ ቁሪን (1998) የተባለው ተመራማሪ በፈላሻነትና ቅማንትነት መደብ አመሠራረት ላይ አጥንቶ በጻፈው የምርምር ሥራው እንዲህ ብሎናል፡- "Kemant traditions assert that tewodros grew up with close relations with Kemant and Spoke their language, while one foreign observer said he may have been of Kemant origin." ስንተረጉመው "የቅማንት የቃል መረጃዎች እንደሚሉት ቴዎድሮስ ከቅማንቶች ጋር በጥብቅ ግንኙነት ያደገ ሲሆን ቋንቋቸውንም ይናገር ነበር፣ እንዲያውም እንደ አንድ የውጭ ሃገር ተመልካች [ቴዎድሮስ] ቅማንት ሳይሆን አይቀርም ይባላል።" በዚህ አባባል ውስጥ ሁለት ነገሮች እናገኛለን። አንደኛው በወቅቱ የሚጠላውንና የሚገለለውን ከመንትነይ ቋንቋ የሚናገር ሰው ቅማንት ካልሆነ በስተቀር አማራ ሊሆን ይችል ይሆን? እንዲያውም ቅማንቱ ራሱ እየተሸማቀቀ ቋንቋው ላለመናገር ሲከጅል በነበረበት በዚያ ዘመን ከማንትነይ ያፍ መፍቻው ካልሆነ በቀር እንዴት ሊናገረው ይችላል? ሁለተኛው ደግሞ ቅማንቱ በአማራው ዘንድ በጣም ሲጠላ በነበረበትና እንደ አረመኔ በሚቆጠርበት ወቅት የትኛው አማራ ነው ከቅማንቶች ጋር አብሮ እንዲያድግ ልጁን አደራ ሊሰጥ የሚሞክረው? በዚህም ቴዎድዎስ ከቅማንት ጋር አብሮ ስላደገ ነው እንጂ አማራ ነበር የሚሉ ሰዎች ከንቱ ክርክር ያበቃለታል ማለት ነው።

***

ራስ ካሳ ሐይሉ ቅማንት ስለ ነበረ በቅማንቶች ዘንድ ትልቅ ክብርና ውዴታ ነበረው። እሱም ቅማንቱን አብልጦ ያምነው ነበር፤ ወገኑ ስለ ነበር። ለዚህም ጀምስ ቁሪን እንዲህ ብሏ "Kemant owed their strategic position to their early support of the revolt of Kassa-Tewodros of Qwara against the kingmakers, ras Ali and his mother, Manan . . . ." ይህም የሚለን ቅማንቶች የቴዎድሮስን የሽፍትነት ጊዜ ሁሉ አግዘውታል። በተለይም የነበራቸውን ገዢ መሬት ተጠቅመው። ጸሐፊው ቀጥሎም አያሌ ቅማንቶች በንጉሡ ወታደራዊ ኃይል ውስጥ የነበረውን የመሳተፍ አጋጣሚ ተጠቅመውበታል። በ1860ዎቹ ቅማንቶች ለወታደራዊ ሕይወት በነበራቸው ፍቅርና የንጉሱን ጦር ሐይል በአብዛኛው ይዘውት ስለበነር ትልቅ ዝና ነበራቸው። ከሰራዊቱም አብዛኛው ቅማንቶች ነበሩ ይለናል። በመሆኑም ቅማንቶች ቴዎድሮስን ከመጀመሪያው እስከ መጨረሻው ደግፈውታል። ወሳኝ ወሳኝ የወታደራዊና አስተዳደራዊ

ቦታዎችን ይዘው ነበር። ለምን ይህ ሁሉ ተደረገ? ብለን መጠየቃችን ግን አይቀርም። መልሱ ደግሞ አለቃ አጽሜ እንቅጩን እንደነገረን ቅማንቶች ወገኖቹ ስለነበሩ ነው። .
.
#Share
Yemane Abadi Mekelle
Birhan Teka
Birhan Berhe